# ኅብረት ለምርጫ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

# በኢትዮጵያ የምርጫ ቅሬታ አሰማም ዘዴ ላይ የተዘጋጀ

# የኅብረት ለምርጫ ፖሊሲ ፍሬ ሃሳብ

ሐምሌ 2015 ዓ.ም

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ማጠቃለያ እና ዋና ዋና ነጥቦች | 4 |
| ዋና ዋና ነጥቦች | 6 |
| የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ | 7 |
| የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሁሉም የምርጫ አስተዳደር ደረጃዎች | 8 |
| በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ የተነሱ ቅሬታዎች | 9 |
| ማጠቃለያ እና ምክረ ሃሳቦች | 10 |

# ዋና ማጠቃለያ



Photo: NEBE



ከምርጫ ጋር በተገናኘ የሚነሱ ቅሬታዎችን በወቅቱ እና በአግባቡ ለመፍታት የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን (Grievance Hearing Committees) በተፈላጊው መጠን መመስረት እና ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ ወሳኝ ነው። የእነዚህን ኮሚቴዎች ውጤታማነት እና ቅልጥፍና ማረጋገጥ የተግባራዊነት መስፈርቶችን ከአቤቱታ አቅራቢዎች መብት ጋር የሚያመዛዝን ተግባራዊ የህግ ማዕቀፍ ማውጣትን ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ እና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ማቋቋሚያ እና አሰራር መመሪያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልል እና በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ደረጃ ባሉ የምርጫ አፈጻጸም መዋቅሮች ላይ ሶስት ሶስት አባላት ያሏቸው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ያቋቋማሉ።

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ (ቦርዱ) በህግ የተቋቋሙትን ኮሚቴዎች በአግባቡ መጠቀም አለመቻሉን የኅብረት ለምርጫ የስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ትዝብት ሪፖርት ያሳያል። በዚህም የተነሳ ቅሬታ አቅራቢዎች (መራጮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎች) ከሕግ ውጪ ለሆኑ አሰራሮች እንደተጋለጡ የኅብረት ለምርጫ ትዝብት ያመለክታል። በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ድምጾችን ከማጣራት እና ከመቁጠር ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችን ፣የፓርቲ ተወካዮችን ከምርጫ ቆጠራ ሂደት ማባረር፣ መራጮችን ማስፈራራት፣ የገዥው ፓርቲ አባላት ጣልቃ ገብነት፣ በተንቀሳቃሽ የምርጫ ታዛቢነት እንዳይሳተፉ በባለሥልጣናት/በአስተዳዳሪዎች መገደብ የመሳሰሉት ቅሬታዎች ቀርበው ነበር።

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሃሳብ በፖሊሲ አውጪዎች በተለይም ቦርዱ በኢትዮጵያ የምርጫ ቅሬታ አሰማም ዘዴ ላይ የፖሊሲ ማሻሻያ ለማድረግ አሳማኝ ሃሳብ ለማቅረብ ያለመ ነው። በዚህ ሰነድ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና ለሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የተለያዩ ምክረ-ሃሳቦች ተሰጥተዋል። በዚህም መሰረት ቦርዱ አሁን በሕግ የተደነገገው የምርጫ ቅሬታ አሰማም ሂደት ካሉበት ተግባራዊ ውሱንነት አንፃር በማሻሻል የቅሬታ አሰማም ሂደቶች ተግባራዊ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል። ፖለቲካ ፓርቲዎች ቅሬታቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁሉንም የሕግ እና የተቋም መስፈርቶች የሚከተሉ እንዲሆኑ አቅማቸውን ማሳደግ። በተጨማሪም የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አባላትን በመመልመል እና በማሰልጠን ለምርጫ ቦርድ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው። ከዚህም ባለፈ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የኢትዮጵያ የምርጫ ቅሬታ አሰማም ዘዴ ሕግን የሚመለከቱ ስልጠናዎችን ለፖለቲካ ፓርቲዎች መስጠት አለባቸው።

# ዋና ዋና ነጥቦች

- የምርጫ አዋጁ እንዲሁም መመሪያው ለቦርዱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በተለያዩ ደረጃዎች እንዲያቋቁም ሕጋዊ ስልጣን የሰጠው ቢሆንም በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ቦርዱ ኮሚቴዎችን በምርጫ ጣቢያ ደረጃ በበቂ ሁኔታ ማቋቋም አልቻለም ነበር። በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ቦርዱ የመራጮች ምዝገባን በ42,585 የመራጮች ምዝገባ ጣቢያዎች እንዲሁም የድምጽ መስጠትን በድምጽ መስጫ ቀን በተቋቋሙ 49,407 የምርጫ ጣቢያዎች አካሂዷል። በአጠቃላይ 555(አምስት መቶ ሃምሳ አምስት) የምርጫ ክልል የነበሩ ሲሆን፣ በሕጉ መሰረት እያንዳንዱ የምርጫ ክልል ውስጥ የሚገኙ የምርጫ ጣቢያ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል። እያንዳንዱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በምርጫው ቀን እንዲሁም በመራጮች ምዝገባ ወቅት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች እና የምርጫ ክልሎች ሶስት አባላትን በማካተት እንደሚቋቋም ያስቀመጠ ቢሆንም፣ በስድስተኛው አጠቃላይ ምርጫ የተቋቋሙት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በአዋጁም ሆነ በመመሪያው በተቀመጠው መሰረት አልነበረም።

- በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ላይ የተነሱ ቅሬታዎችን በፌደራል ደረጃ ለመፍታት ተሞክሯል። ቦርዱ ቅሬታዎችን ተቀብሎ ውሳኔዎች ለመስጠት ባደረገው ጥረት ላይ ምስክሮችን ከመስማት ጋር ተያይዞ የቋንቋ ማነቆዎች፣ የማስረጃ ምዘና ክፍተቶች እንዲሁም የጊዜ ገደብ መጣበብ ጋር የተገናኙ ተግዳሮቶች አጋጥመውታል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በይግባኝ ወደ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የቀረቡ በርከት ያሉ ቅሬታዎች በሕግ የተቀመጠውን የ10 ቀን የጊዜ ገደቡ ከማለፉ ማለቂ ጋር በተያያዘ በይርጋ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ እንደተደረጉ ተመላክቷል።

# ምክረ-ሃሳቦች

- ቦርዱ በየደረጃው የሚያቋቁማቸው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የሚቀርቡላቸውን ቅሬታዎች በአግባቡ እና በብቃት መፍታት እንዲችሉ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ላይ ያለውን የህግ ማእቀፍ እንደገና መቃኘት ይኖርበታል።
- ፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ወቅት የሚኖሯቸውን ቅሬታዎች ለማቅረብ ማሟላት ያለባቸውን መስፈርቶችን በሚገባ መረዳት አለባቸው።
- ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ቦርዱ ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ምልመላ እና ስልጠን ጋር ተያይዞ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ሊያግዙ ይገባል።




Photo: NEBE

# መግቢያ

ስድስተኛው የኢትዮጵያ ጠቅላላ ምርጫ በሰኔ 2013 እንዲሁም በመስከረም 2014 ዓ.ም ተካሂዷል። የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በኢፌደሪ ህገ መንግስት እና የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/19 በተሰጠው ስልጣን ነፃ እና ገለልተኛ የምርጫ ስርዐት በመከተል ዜጎች ተወካዮቻቸውን በፍትሃዊ እና ሰላማዊ ምርጫ እንዲመርጡ በማስቻል በነጻነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸውን እንዲጠቀሙ ታልሞ የተቋቋመ ድርጅት ነው።[1]

ቦርዱ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 በተለያዩ ደረጃዎች ከምርጫ ጋር የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመቀበል የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በምርጫ ጣቢያ፣ የምርጫ ክልል እና በክልል የቦርዱ ጽ/ቤት የማቋቋም ስልጣን አለው።[2] ቅሬታ ሴሚ ኮሚቴ የተቋቋመው በምርጫ ጣቢያዎች፣ በምርጫ ክልሎች እና በምርጫ ቦርድ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚቀርቡ ቅሬታዎች ላይ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ለመስጠት ነው።[3]

ከአዋጁ በተጨማሪ በምርጫ ጣቢያ፣ በምርጫ ክልልና በክልል ደረጃ የተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት እና የአሰራር ማዕቀፍ እንዲሁም የድርጅትና የአሰራር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 10 ላይ በዝርዝር ተቀምጧል። ምርጫ ቦርድ በህጋዊ መንገድ የተቋቋመውን የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ (GHC) በአግባቡ መጠቀም አለመቻሉን የኀብረት ለምርጫ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ሪፖርት አረጋግጧል። በዚህም ምክንያት በቅሬታ አቅራቢዎች (መራጮች፣የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሌሎችም) ላይ የደረሱ ህገ-ወጥ ድርጊቶች እንደነበሩ ሪፖርቱ አሳይቷል።

# የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ

በእያንዳንዱ ምርጫ የምርጫ ቅሬታዎችን በወቅቱ እና በአግባቡ ለመፍታት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ውጤታማነት ወሳኝ ነው። የእነዚህን ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ውጤታማነት እና ቅልጥፍና ማረጋገጥ መሬት ላይ ተግባራዊ የሚደረግ የህግ ማዕቀፍን መዘርጋት እንዲሁም ከቅሬታ አቅራቢዎች መብት ጋር ማመዛዘንን ይጠይቃል። የኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ እና የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቋቋሚያና አሰራር መመሪያ በምርጫ ጣቢያዎች፣ በምርጫ ክልል እና በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች  እያንዳንዳቸው ሶስት አባላትን የያዙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችያ ያቋቁማሉ።

በሰኔ 2013 ዓ.ም እና መስከረም 2014 ዓ.ም ለተካሄደው ስድስተኛውን ጠቅላላ ምርጫ የመራጮች ምዝገባ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደትን የሚያካሂዱ 50,000 ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እና 673 የምርጫ ክልሎችን[4] ለማደራጀት ታቅዶ በእያንዳንዱ መዋቅር 3 አባላትን የያዙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን የሚያቋቁመው የሕግ ማዕቀፍ በተግባር ቦርዱ በአጠቃላይ 150,000 እና 2,019 የሚሆኑ አባላት ያላቸው የምርጫ ጣቢያ እና የምርጫ ክልል (በተከታታይ) የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እንዲቀጥር፣ እንዲያሰለጥን እና እንዲያሰማራ የምርጫ ህጉ ለምርጫ ቦርድ ኃላፊነት ይሰጣል። በየምርጫ ጣቢያው ተቀጥረው፣ ሰልጥነው እንዲሰማሩ ከሚደረጉት በተጓዳኝ 3 የምርጫ አስፈፃሚዎች ጨምሮ በጠቅላላው በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ የሚያስፈልጉ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞችን (የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትን ጨምሮ) ቁጥር ወደ 300,000 ከፍ ያደርገዋል።

1 National Electoral Board of Ethiopia. (2019). Establishment Proclamation No.1133/2019. Retrieved from https://chilot.me/2019/08/21/national-electoral-board-of-ethiopia-establishment-proclamation-no-1133-2019/
2 Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2019). The Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Elections' Code of Conduct Proclamation 1162/19. Article 7. Retrieved from https://chilot.me/wp-content/uploads/2019/09/The-Ethiopian-Electoral-Political-Parties-Registration-and-Elections-Code-of-Conduct-Proclamation-No.-1162-2019.pdf
3 Alemu, G. (2021). Ethiopia's 2021 elections: rules, actors, and mechanisms. African Journal of Democracy and Governance, 8(1), 1-15. Retrieved from https://www.ajdg.co.za/index.php/volume-8-issue-1-june-2021/196-ethiopia-s-2021-elections-rules-actors-and-mechanisms
4 National Electoral Board of Ethiopia. (n.d.). Polling Stations. Retrieved July 4, 2023, from https://nebe.org.et/en/polling-stations

አፈጻጸም ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን መጠን ከግንዛቤ በማስገባት፣ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች 3 አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም ያቀደው የህግ ማእቀፍ በመጠኑ የተጋነነ ይመስላል። በኢትዮጵያ የምርጫ ቅሬታ ሰሚ የህግ ማዕቀፍ የዜጎች የመምረጥና የፍትህ ተጠቃሚነት መብት እንዲከበር እና እንዲፈጸም ያለመ ቢሆንም፣ ምርጫ ቦርድ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ላይ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ማደራጀት አለመቻሉ በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች ላይ የምርጫ ቅሬታዎችን ለመፍታት እንቅፋት ሆኑዋል።

በመሆኑም በአጠቃላይ የምርጫን ተዓማኒነት ለማስጠበቅ አስፈላጊ የሆኑትን የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተግባር ለማረጋገጥ በምርጫ አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ኮሚቴው በምርጫ ጣቢያ ደረጃ 3 አባላት ሊኖሩት እንደሚገባ የሚደነግገውን የህግ ማዕቀፍ እንደገና መከለስ ይኖርበታል።

# የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች፡ ተግባራት፣ ሂደቶች እና የጊዜ ሰሌዳዎች

## የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተግባራት

የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በመራጮች ምዝገባ፣ በእጭዎች ምዝገባ እንዲሁም በድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የመቀበል ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል።

## በመራጮች ምዝገባ ሂደት ውስጥ ያሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተግባራት

ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ በማንኛውም ሰው ወይም በፖለቲካ ፓርቲ የሚነሱ ቅሬታዎች በምርጫ ጣቢያ ደረጃ ለሚቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ይቀርባሉ። እነዚህ በምርጫ ጣቢያ ደረጃ ያሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በ5 ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው ተግባራዊነት ባላቸው የምርጫ ሕጎች ላይ ተደንግጓል። ነገር ግን ኮሚቴዎቹ በተሰጠው የ5 ቀን ጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ መስጠት ካልቻሉ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ይግባኝ ለምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ5 ቀናት የጊዜ ገደብ ማስገባት ይችላል። ይግባኝ የቀረበለት የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ5 ቀን ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን በጹሁፍ እንዲሰጥ ይገደዳል። አሁንም፣ ኮሚቴው በተሰጠው የ 5 ቀን የጊዜ ገደብ ውሳኔ ያልሰጠ ከሆነ ወይም በውሳኔው ቅር መሰኘት ካለ፣ በ5 ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ለፌደራል ወይም ለክልል ፍርድ ቤት ይቀርባል።

## በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት ውስጥ ያሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተግባራት

ከዕጩዎች ምዝገባ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቅሬታዎች የሚቀርቡት ለምርጫ ክልል የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ነው። የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የሚደርሷቸውን ቅሬታዎች በገቡ እስከ አምስተኛው ቀን ባለው ጊዘ ውሳኔ መስጠት እንዳለባቸው ተጠቅሷል። በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተደሰቱ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ገለልተኛ እጩ ተወዳዳሪዎች በሰባት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለቦርዱ የክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ሲኖር ወይም ኮሚቴው በሰባት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ሳይሰጥ ሲቀር ቅር የተሰኘው አካል በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ውሳኔ የመስጠት ግዴታ ላለው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል።

### ድምጽ እንዳይሰጡ በመከልከል ምክንያት ለሚነሱ ቅሬታዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተግባራት

በድምጽ መስጠት መከልከል ምክንያት ቅሬታ ያላቸው መራጮች በምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታቸውን የማቅረብ እና ውሳኔ የማግኘት መብት አላቸው። ስለሆነም ኮሚቴው ጉዳዩን መርምሮ መራጩ እንዲመርጥ እንዲፈቀድለት ብሎም ጉዳዩን ወደ ምርጫ ክልል አስመራጭ ጽህፈት ቤት ለውሳኔ ይልካል። ማንኛውም በዚህ መልኩ ጊዜያዊ ድምጽ የሰጠ እና በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ውሳኔ ያልተደሰተ ሰው ማመልከቻውን ለሚመለከተው የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ወድያውኑ ማመልከት አለበት። በተጨማሪም ማንኛውም የሌላ ሰው የመምረጥ መብት ላይ ቅሬታ ያለው ግለሰብ በተመሳሳይ አሰራር/ ሂደት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

### በድምጽ ቆጠራ እና ውጤት አገላለጽ ምክንያት ለሚነሱ ቅሬታዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተግባራት

ከድምጽ ቆጠራ እና ውጤት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ቅሬታዎች መቅረብ ያለባቸው ለምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ነው። በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ለምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔውን ይግባኝ ማለት ይችላል፣ ይግባኝ የቀረበለት ኮሚቴም ውሳኔውን በሁለት ቀን ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል። ማንኛውም የምርጫ ክልሉን ውሳኔ የሚቃወም አቤቱታ፣ኮሚቴው ውሳኔ በሰጠ በአምስት ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ አቤቱታ አቅራቢው ቅሬታውን ለቦርዱ ማስገባት ይኖርበታል። ቦርዱ ቅሬታውን መርምሮ በ10 ቀናት ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት። በሌላ በኩል በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ካለ ቅሬታ አቅራቢው የቦርዱን ውሳኔ በተቀበለ በ 10 ቀናት ውስጥ ሁለተኛ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ውሳኔውን ከአንድ ወር ባነሰ ጊዜ ውስጥ መስጠት ይገባዋል።

# በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ የተነሱ ቅሬታዎች

በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ በመራጮች ምዝገባ፣ በምርጫ ቀን እና በድህረ ምርጫ ጊዜያት በርከት ያሉ ቅሬታዎች ተስተውለዋል። ምርጫ ቦርድ በሶማሌ ክልል በተካሄደው የመራጮች ምዝገባ ሂደት ላይ ከፖለቲካ ፓርቲዎች በደረሰው ቅሬታ በሶማሌ ክልል የተካሄደውን ምርጫ መርምሮ እንዲቆም አድርጓል። በሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በወላይታ ዞን በሚገኙ ስድስት የምርጫ ክልሎች የተወዳደሩ ፓርቲዎች በድምሩ 476 የምርጫ ጣቢያዎች በድምፅ አሰጣጥና ቆጠራ ሂደቶች ላይ የተስተዋሉ ችግሮችን በመጥቀስ ቅሬታቸውን ለቦርዱ አቅርበዋል። እነዚህ ቅሬታዎች የቀረቡትም ሆነ የተስተናገዱት በምርጫ ጣቢያ ደረጃዎች ባሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አልነበረም። ቅሬታዎቹ ከቀረቡ በኋላ ምርጫ ቦርድ በወላይታ ዞን የተካሄደው ምርጫ እንዲታገድ እና በመስከረም ወር 2014 ዓ.ም ምርጫ እንዲካሄድ ወስኗል።

ኅብረት ለምርጫ በድህረ ምርጫ ከባቢ ባደረገው ትዝብት የቅሬታ አያያዝ ሂደቶች በምርጫ የህግ ማዕቀፍ ከተቀመጡት ሂደቶች ጋር የተጣጣሙ እንዳልነበሩ ተመልክቷል። ምርጫ ቦርድ በአዲስ አበባ ከተማ በፌዴራል ደረጃ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ስካይ ላይት ሆቴል በተቋቋመ ጊዜያዊ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የተስተናገዱበትን አሰራር ተከትሎ ነበር። ይህ የቅሬታ አሰማም በህግ ከተገለጸው ውጭ ከመሆኑም ባለፈ ከአገር አቀፍ ደረጃ ወደማዕከል የመጡ ቅሬታዎች የተሰሙት የስልክ ጥሪዎችን በመጠቀም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ክፍተቶችን የተስተዋሉበት ነበር።

ድምጾችን ከማጣራት እና ከመቁጠር ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችን ፣የፓርቲ ተወካዮችን ከምርጫ ቆጠራ ሂደት ማባረር፣ መራጮችን ማስፈራራት፣ የገዥው ፓርቲ አባላት ጣልቃ ገብነት፣ በተንቀሳቃሽ የምርጫ ታዛቢነት እንዳይሳተፉ በባለሥልጣናት/ በአስተዳዳሪዎች መገደብ የመሳሰሉት ቅሬታዎች ከቀረቡባቸው ሁኔታዎች ከብዙ በጥቂቱ ይጠቀሳሉ። የኅብረት ለምርጫ አጠቃላይ የምርጫ ትዝብት ሪፖርት እንዳስቀመጠው፣

ከምርጫ ቦርድ የህግ ክፍል በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በሰኔው ምርጫ ወቅት በ212 ምርጫ ክልሎች በ31 የፖለቲካ ፓርቲዎች እና በ6 እጩዎች በሰኔው ምርጫ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን፣ በመስከረሙ ምርጫ በ25 የምርጫ ክልሎች በ24 ገለልተኛ እጩዎች እና በስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅሬታ አቅርበዋል። ምርጫ ቦርድ እነዚህ ቅሬታዎች ከደረሱት በኋላ በማስረጃ ማነስ ምክንያት ቅሬታዎቹን ውድቅ አድርጓል። ብሎም ይግባኝ ሰሚ ችሎቶቹ በሕጉ የተደነገገውን የጊዜ ገደብ ህግ ባለማሟላታቸው የቀረቡትን ይግባኝ አቤቱታዎች ውድቅ አድርገዋል።

# በኢትዮጵያ ያለው የምርጫ ቅሬታ አሰማምን ለማሻሻል የቀረቡ ምክረ-ሃሳቦች

ቅሬታዎች በተቀላጣፈ እና ፍጥነት ባለው መንገድ የሚስተናገዱበትን ጠንካራ የቅሬታ አሰማም ሂደት ማበጀት ያስፈልጋል። ምርጫዎች የሚከናወኑበትን የተጣበበ የጊዜ ሠሌዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት በምርጫ ወቅት የሚዘገጉ የቅሬታ አሰማም ሂደቶች ቅሬታዎችን በወቅቱ ለመፍታት የሚያስችሉ ወጥ የሆነ የተዋረድ መዋቅሮችን መንደፍ ያስፈልጋል።

አዋጅ ቁጥ 1162/2019 እና ተፈፃሚነት ያላቸው መመሪያዎች አስተዳደራዊ የሆኑ በመራጮች ምዝገባ፣ በዕጩዎች ምዝገባ፣ በድምጽ አሰጣጥ እና ወዘተ የምርጫ ሂደቶች ላይ ያሉ የምርጫ ሂደቶች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በተለያዩ ደረጃዎች የሚፈቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል።

ይህን ቁጥር በእያንዳንዱ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ቢያንስ ሶስት የምርጫ አስፈፃሚዎች እንዲገኙ ከተቀመጠው ድንጋጌ ላይ ስንጨምረው  ቦርዱ ለምርጫ አስፈፃጽም የሚያስፈልገው የሰራተኛ ቁጥርን ወደ 300,000 ከፍ ያደርገዋል። ይህን አዳጋች የሚያደርገው ደግሞ የሚቋቋሙት የምርጫ ጣቢያዎች በብዛት በገጠራማ አካባቢዎች መሆኑ ነው። 150,000 ሰዎችን መመልመል የቦርዱን አቅም የፈተነ ከፍተኛ የሎጂስቲስክ እክል ፈጥሯል። በተጨማሪም ለ150,000 የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በምርጫ ሕጎች  እኛ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባልነታቸው ላይ ያሉ ተግባር እና ኃላፊነቶችን ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ስልጠና መስጠት ሌላኛው ፈታኝ ተግዳሮት ነው። ከዚህ በላይ ይህን ያክል ቁጥር ላላቸው ሰዎች ምልመላ እና ስልጠና የሚወጡ ክፍያዎች ከበጀት አኳያም ጫና ያሳድራሉ። በዚህ ትንተና ላይ በመመርኮዝ ኅብረት ለምርጫ የሚከተሉትን ምክረ-ሃሳቦች ያቀርባል።

የኅብረት ለምርጫ የስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ትዝብት እንደሚጠቁመው በጥቅሉ አብዛኛዎቹ የምርጫ ቅሬታ አፈታት ሂደቶች የምርጫ ሕግጋትን ያልተከተሉ ነበሩ። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች እና የምርጫ ክልሎች ለማቋቋም የሚያቅደው የሕግ ማዕቀፍ ውጤታማ ያልነበረ እና ከመጠን ያለፈ ምኞትን ያዘለ ነው። ምንም እንኳን በምርጫው ቀን ተቋቁመው በርካታ ቅሬታዎችን በመቀበል ያስተናገዱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የነበሩ ቢሆንም፣ በየምርጫ ጣቢያው ይቋቋማሉ ተብለው ሲጠበቁ የነበሩት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ብዙዎቹ የምርጫ እለት ለተነሱ እንዲሁም የምርጫው ውጤት ይፋ ከሆነ በኋላ የነበሩ ቅሬታዎችን ለመቀበል በትክክል አለመቋቋማቸውን የኅብረት ለምርጫ ትዝብት አመላክቷል። በተጨማሪም በምርጫ ጣቢያም ሆነ በምርጫ ክልል የነበሩት ኮሚቴዎች ውጤታማ አልነበሩም። በአጠቃላይ ምርጫ ቦርድ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ በህግ የሚቋቋመውን የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በምርጫ ጣቢያዎች፣ በምርጫ ክልሎች እና በክልል ደረጃ መጠቀም አልቻለም ነበር።

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ (ምርጫ ቦርድ)

- የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ደረጃ ማቋቋም ከሕግ፣ ከተቋም፣ ከዕቅድ እና ከአፈፃጸም ጋር ያሉ ተግዳሮቶችን ማጥናት እና መለየት ያስፈልጋል።
- ቦርዱ 50,000 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ከማቋቋሙ ጀርባ እንዲሁም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ካለማቋቋሙ ጀርባ ያሉ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን መፈተሽ አለበት።
- ከኢትዮጵያ ጋር ተነፃፃሪ የዕድገት ደረጃ፣ የቅሬታ አሰማም ሂደቶች፣ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ብዛት እና አገራዊ የመሰረት ትምህርት ደረጃ ላይ ያሉ አገራትን ተሞክሮ በመቅሰም ልምዶችን ወደኢትዮጵያ ማምጣት ይኖርበታል።
- ከላይ ያለው ትንተና እንደሚያሳየው በምርጫ ሕጉ የተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች  በተጋነነ ዕቅድ ላይ የተመሰረቱ እና በተግባር ለመፈጸም አዳጋች ናቸው።በዚህም መሰረት ቦርዱ አሁን ባለው የቅሬታ አሰማም ሂደት ላይ የሕግ ማሻሻያ ሊያደርግ ይገባል።

## የፖለቲካ ፓርቲዎች

- ቅሬታቸውን በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁሉንም የመርህ እና የሥነ ሥርዓት መስፈርቶች የሚከተሉ እንዲሆኑ አቅማቸውን ማሳደግ።
- የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ላይ ባለው የቅሬታ አሰማም ሂደት ላይ ስልጠናዎችን ለፖለቲካ ፓርቲዎች መስጠት አለበት።

## የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች

- የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አባላትን በመመልመል እና በማሰልጠን ለምርጫ ቦርድ ድጋፍ ማድረግ።

# Endnotes/ References

1. CECOE. (2022). Final Observation Report: Sixth National and Regional Elections of Ethiopia. May 2022. Retrieved from https://www.africa-elections.org/home/country-profiles/ethiopia/final-observation-report-sixth-national-and-regional-elections-of-ethiopia-may-2022/
2. Alemu, G. (2021). Ethiopia's 2021 elections: rules, actors, and mechanisms. African Journal of Democracy and Governance, 8(1), 1-15. Retrieved from https://www.ajdg.co.za/index.php/volume-8-issue-1-june-2021/196-ethiopia-s-2021-elections-rules-actors-and-mechanisms
3. Federal Democratic Republic of Ethiopia. (2019). The Ethiopian Electoral, Political Parties Registration and Elections' Code of Conduct Proclamation 1162/19. Retrieved from https://chilot.me/wp-content/uploads/2019/09/The-Ethiopian-Electoral-Political-Parties-Registration-and-Elections-Code-of-Conduct-Proclamation-No.-1162-2019.pdf
4. National Electoral Board of Ethiopia. (2019). Establishment Proclamation No.1133/2019. Retrieved from https://chilot.me/2019/08/21/national-electoral-board-of-ethiopia-establishment-proclamation-no-1133-2019/

በ6ተኛው ጠቅላላ ምርጫ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም(NDI) የኅብረት ለምርጫን  የዜጎች ምርጫ ትዝብት ተግባራትን የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይህ የፖሊሲ ምክረ - ሃሳብ ታትሞ ሊወጣ የቻለው እና የታተመው በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (USAID) በኩል ከአሜሪካ ሕዝብ በተበረከተ ቸር እገዛ ሲሆን ይዘቱ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ) ኃላፊነት እንጂ የUSAID፣ የአሜሪካ መንግስት አመለካከት የሚያንፀባርቁ አይደሉም።

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ) በኢትዮጵያ ለሚደረጉ ምርጫዎች የፖሊሲ፣ የህግ እና የተቋማዊ ማሻሻያዎች ምቹ ሁኔታን ለመደገፍ ይህንን የፖሊሲ ፍሬ ሃሳብ አዘጋጅቷል። ኅብረት ለምርጫ፤ በምርጫ ሂደት የህግ ማዕቀፎች እና የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ለማበረታታት በእነዚህ ህትመት ውስጥ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ፣ በፖሊሲ ላይ ያተኮረ ትንተና እንዲሁም ምክረ -ሃሳቦችን ተጠቅሟል፡፡

**የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት  ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ**

ስድስት ኪሎ፣ ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢኒስቲቲውት ሕንጻ 2ኛ ወለል
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

+251 11 811 1455
www.cecoe.org
info@cecoe.org
twitter: @cecoeEth
facebook: CECOE21